የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ማህበራት ጉባኤ (ኢሕማጉ)
Congress of Ethiopian Civic Associations (CECA

# ሕዝባዊ እምቢተኝነት ለዲሞክራሲ ውልደት ብሥራት ነው

የኢ.ሕ.ማ.ጉ. ይፋዊ መግለጫ

ጥቅምት 20 ቀን 2017 ዓም

አምባገነናዊና ከፋፋይ ሥርዓትን በሕዝባዊ ንቅናቄ ለመገርሰስ የሚደረግ ትግል ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ በሶስት ምሰሶዎች ላይ መቆም ይኖርበታል። የምሰሶዎች አንዱ እግር ገጠር-ተኮር የሆነ የትጥቅ ትግል ነው፤ ሁለተኛው መዳረሻንና የመዳኘ አቅጣጫን ጥርት አድርጎ የሚያሳይ የፖለቲካ ስልት ያማተረ ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ ከተማ-ተኮርና በሰላማዊ የሕዝባዊ እምቢተኝነት የታጀበ እንቅስቃሴ ነው። በአማራ ፋኖ የተቀሰቀሰው ትጥቅ ትግል ባልተለመደ የድል ፍጥነትና በተለመደው የትግል ዲሲፕሊን አውዱን እያሰፋ መጥቶ ሁለተኛውንና ሶስተኛ እግሮቹን ማጠናከር ውስጥ መግባቱ ተስፋ ሰጪ ነው። ይሁን እንጂ፤ ንቅናቄው በሶስት ጠንካራ ምሰሶዎች ላይ ካልተተከለና አማራ ያልሆነው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ሁሉ ንቅናቄውን በባለቤተኝነት ተቀላቅሎ ሃገራዊ መልክ ካልሰጠው ወደ አንድነትና ዴሞክራሲያዊ እኩልነት መሸጋገር እንደማይቻል በዚች መግለጫ ስጋታችንና ተስፋችንን ለማካፈል እንወዳለን።

ተስፋችን በማይነጥፈው ኢትዮጵያዊነት አብሮነታችን ላይ የተገነባ ሲሆን፤ የስጋታችን መንስኤዎች በሃገራችን ኢትዮጵያ፤ ከከፋፋይ ሕገ መንግሥት፤ የአስተዳደርና ፍትኅ ተቋማት ደካማነት ሌላ፤ በውጭ አፍራሽ ሃይሎች ጣልቃ ገብነትና፤ ለወቅቱ መጣኝና ተገቢ የትግል ስልቶችን ባለመጠቀም ብዙ የለውጥ እድሎች አምልጠውናል። ይህም ክስተት ሕዝባችንን ለማያባራ ሠላም ማጣት፤ ማለቂያ የሌለው እንግልትና ስቃይ ረሃብ መሰደድና የሞት አደጋ ላይ ጥሎት ይገኛል። በአንፃሩ፤ የትሕነግም ይሁን የብልፅግና መሪዎች መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ይህንኑ ከፋፋይ ሕገ መንግስት በመከተል ችግሩ ይበልጥ እንዲባባስና የሕዝብ የርስ በእርስ ግጭት እንዲጨምር በማራገብ ለመሄድ የመረጡ በሚመስል ሂደት አሁን ያለንበት ሀገራችንን ወደ መበታተን አደጋ ላይ አድርሷታል። ለዚህም የአገዛዝ ዕድሚያቸውን ማራዘሚያ አድርገው የመረጡት፤ አንዱን ብሄር/ጎሳ ጭራቅ ሌላውን ብሄር/ጎሳ መልአክ አድርጎ በመሳል የእርስ በእርስ ፀቡ እንዳይበርድ ማራገብ ነው።

ከደርግ አስተዳደር ጀምሮ ጨቋኝ፤ ነፍጠኛና ገዳይ ችግር ፈጣሪ ተብሎ በሀሰትና በፈጠራ ታሪክ የተፈረጀውና ከፍተኛ ጥቃት ሲፈጸምበት ከቆየው የአማራው ህብረተሰብ የዚህ ዕርስ በዕርስ ግጭት ሰለባ እንዲሆን የተመረጠ ቢሆንም ከአብራኩ የወጡ

የፋኖ አርበኞች ዓለምን ባስደነቀ መልኩ በአራቱም የአማራ ክፍለ ሃገራት በደሉ በቃን በማለት እራሳቸውን በትጥቅና በአስተዳደር አደራጅተው የመንግስቱን እርካብ ለመረከብ ዝግጁነታቸውን አሳይተዋል። የብልጽግና መንግሥት ተብዬውም በአንድ በኩል በአየርና በመሬት ሠራዊቱን አሰማርቶ ንጹሃንን ያለርህራሄ በመጨፍጨፍ ላይ ቢሆንም፤ ከህዝብ ተውጣጥቶ በህዝብ ታቅፎና ተደግፎ የሚዋጋው አርበኛ ወይም ፋኖ እነሆ በአንድ ዓመት ውስጥ የመንግስቱን ሠራዊት በተለይም በአማራው ገጠር አካባቢ ሚች፤ ቁስለኛና ምርኮ እያደረገው ይገኛል። ይህን የድል በድል ጉዞ የታዘበ የከተማው ነዋሪ ድጋፉን በማያወላውል የሕዝብ እምቢተኝነት ተቀላቅሎታል።

ይህ ድጋፍ እያደገ መጥቶ፤ በቅርቡ ሕዝብ በተለያዩ አካባቢዎች ሕዝቡ የፍራቻ ቆፈኑን አሽቀንጥሮ ጥሎ አደባባይ በመውጣት ብሶታቸውንና የመንግሥት ለውጥ ፍላጎታቸውን በገሀድ በመግለፅ የሕዝብ እምቢተኛነቱ የትግል ዘርፍ በየከተሞች እንዲቀጣጠል ምሣሌ ሆነዋል። በቅርቡም በደሴ ከተማ ሕዝቡ ግልብጥ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የብልጽግናው መንግሥት ስልጣኑን ለህዝብ እንዲያስረክብ በድፍረት የጠየቀበትን ስናስታውስ፤ ቀደም ብሎ በሰሜን ሸዋ የሚገኙ የኦሮሞ ሕብረተሰብ አባላት የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአካባቢው ባህል መሠረት ለመቋቋም ያቃጣቸው የአስተዳደርና የፍትኅ ችግር ሲገጥማቸው ሞፈርና ቀንበር ተሸክመው ጦርነቱ እንዲቆም ብሶታቸውን በመግለፅ እንደድሮው በኢትዮጵያዊነት ዜግነት በፍቅር አብረን እንሁን በማለት ያስተጋቡበት ደማቅ የሕዝብ ተሳትፎ የታየበት ነበር። በድሬደዋና ጅጅጋም እንደዚሁ በተለይም የኦሮምያ ብሄርተኞች የይገባኛልና የመስፋፋት ጥያቄ የተነሳ ነዋሪው በተለያዩ መንገዶች አማካኝነት ብሶቱንና የተቃውሞ ድምፁን እየገለጸ ይገኛል። የክልሉ አስተዳደርም ከማእከላዊ ፌደራል አገዛዙ ጋር ባለው ቅሬታ የተነሳ ህዝቡ አልፎ አልፎ ብሶቱን በአደባባይ ከመግለጽ አልተቆጠበም። የሕዝብ እምቢተኝነቱ በአደባባይ እየጎላ ሲመጣ፤ ይመራሉ ወይም ይሳተፋሉ ተብለው የተገመገሙ ምሁራኖችና ወጣቶች እንደ አዲስ አበባ መሰል ከተሞች እየታፈሱ ለግፍ እስር ተዳርገዋል፣ እየተዳረጉም ናቸው።

በጦርነትም ይሁን በተለያየ የሕዝብ ሰቆቃ ኑሮ የመረረው ሕዝብ ግፍ ሲደራረብበት ያለማንም ጎትጓች በአገዛዙ ላይ መነሳት አይቀሬ ነው። ለምሣሌ፤ ትሕነግ በቀሰቀው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ብቻ የዓለም አቀፍ አቀፍ ሚድያዎች እንደዘገቡት ቢያንስ ከስምንት መቶ ሺህ ያላነሰ ወገን ህይወቱን በአጣበት ጦርነት፤ በመቀሌና በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች ብሶታቸውን ለመግለጽ አሁን ድረስ አደባባይ እየወጡ ነው።

በጠቅላላው በሃገራችን በሚገኙ ከተሞች የአማራ ዘርን በመጤነት ፈርጀው ከየቦታው ለማፈናቀልና ለማጽዳት በሚደረገው የብልጽግና እኩይ ተግባር የተነሳ በሚሊዮኖች የሚቀጠር ወገናችን ቁጣ ገንፍሎ አደባባይ በመውጣት የብልጽግናን መዋቅር ከስሩ መንግሎ ለመጣል ምንም ዓይነት ሃይል ሊያስቆመው አይችልም ብንል ስህተት አይሆንም። ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ተፈጻሚነቱ የጊዜ ጉዳይ ነው እንላለን።

ሃገሪቷን ከገባችበት አረንቋ በዘላቂነት ለማውጣት አማራ ያልሆነውና በኢትዮጵያዊነቱ ያገባኛል የሚለው ሁሉ ታሪካዊና ዜጋዊ ግዴታ አለበት፤ መብቴን አክብሩ ከማለት ባሻገር የንቅናቄው ሙሉ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበታል። በስርዓቱ ተበደልኩ የሚል ሁሉ በገጠር ትጥቅ ትግል፣ በከተማ ደግሞ የሕዝብ እምቢተኝነት ትግል እኩል ተካፋይነት ግድ ይላል። ዲያስፖራውም ዘርና ሃይማኖት ሳይለያይ በአንድ ሰንደቅ አላማ ስር ተሰልፎ አገር አቀፍ ትግሉን መርዳት አለበት።

ከራሳችን የቅርብ የፖለቲካ ታሪክ የምንማራቸውን ሁለት ትምህርቶችን ልብ እንበል። ያልተገራ ታጣቂ ኃይል በድል አጥቢያ “ታንኩም የኔ፣ ቤተመንግስቱም የኔ፣ ባንኩም የኔ” ማለቱ አይቀሬ ስለሆነ የከተሜው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ትግሉን ከማገዝ አልፎ አምባገነናዊነት እንዳያንሰራራ ማነቆ ይሆናል። ቀጥሎም አማራ ለብቻው ዘግናኝ መስዋዕትነት ከፍሎ ያመጣውን ድል ሳይታገሉ እኩል ልካፈል ማለት ግብዛዊ የበይ ተመልካችነት ነው።

መብትና ግዴታ መንትዮዎች ናቸው። ስለዚህ እጅ ለጅ ተያይዘን አገራችንን በጋራ እናድን፤ እናዘምን። በስጦታ ያገኘነው ዲሞክራሲ በንዝህላልነት ይቀማልና ዘላቂ ባለቤትነትህን በጀግንነትህ አስመስክረህ ተጎናፀፍ። አልበገሬ ነፃ ኢትዮጵያዊ ማለት ሌላ ትርጉም የለውም!!